# የማረፊያ ቦታ ለሚፈልግ አንድ ሰው ሀብቶችን እየፈለግኩ ነው

## በኮቪድ-19 ወቅት መጠለያዎች አሁንም ክፍት ናቸው?

አዎ፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ መጠለያዎች በኮቪድ-19 ወቅት ክፍት ይሆናሉ። ለአሁን መረጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of Human Services) ድረ ገጽን ይመልከቱ።

## ከአንድ ሰው ጋር ማውራት እፈልጋለሁ። ለማን መደወል እችላለሁ?

- ይህ ለህይወት አስጊ ድንገተኛ ነገር ከሆነ፣ 911 ላይ ይደውሉ።
- ምግብ ወይም መጠለያ ባስቸኳይ ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ፣ በቀን 24 ሰዓት በሳምንት ደግሞ ሰባቱንም ቀናት ክፍት የሆነውን የዲሲ መጠለያ በ (202) 399-7093 የስልክ መስመር ላይ ይደውሉ። የስልክ መስመሩ በ United Planning ድርጅት የሚንቀሳቀስ ሲሆን መጠለያ እንዴት እንደሚፈለግ ወይም በከባድ የአየር ጠባይ ወቅት ወደ ማሞቂያ ወይም ማቀዝቀዣ ማእከል እንዴት ነፃ ጉዞ እንደሚደረግ መረጃ አለው፡፡
- እንዲሁም ታዳጊዎች (ከ 11-18 አመት እድሜ) የደህንነት ቦታ የስልክ መስመርን በ (202) 547-7777 ላይ መደወል ይችላሉ። የስልክ መስመሩ በቀን 24 ሰዓት በሳምንት ደግሞ ሰባቱንም ቀናት ክፍት ክፍት ነው እንዲሁም በ Sasha Bruce Youthwork ድርጅት ይመራል።
- እንዲሁም ስለከተማ አገልግሎቶችና ስለድንገተኛ መጠለያዎች መረጃ ለመጠየቅ በ 311 ላይ መደወል ይችላሉ

## አንድ ሰው አዳሩን የሚያሳልፍበት ቦታ የት ሊያገኝ ይችላል?

በአስቸጋሪ ጊዜ ነዋሪዎች በተቻለ መጠን ምቾት እንዲሰማቸው ለመርዳት፣ በርካታ አይነት የሚገኙ መጠለያዎች አሉ፡

- የድንገተኛ መጠለያ የሚፈልጉ ግለሰቦች ይህንን የወንዶች ዝርዝር- ወይም የሴቶች ብቻ የሆነ መጠለያ ማጣቀስ ይችላሉ።
- ከ 16 እስከ 24 አመት እድሜ ውስጥ ያሉ ታዳጊ ወጣቶች በዲሲ የመንግስት ሀብት ገጽ ላይ ያሉ LGBTQ+ የሚደግፉ እንዲሁም ነፍሰ ጡር/ወጣት ሴቶችን ያቀፉ በርካታ መጠለያዎችን ሊያገኙ ይችላሉ።
- ከ 11 እስከ 17 የሆናቸው መጠለያ የሚፈልጉ ልጆች ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ የስልክ መስመርን በ (202) 547-7777 ላይ መደወል ወይም በ Sasha Bruce ቤትመሄድ ይችላሉ።
- መጠለያ የሚፈልጉ ቤተሰቦች የVirginia Williams የቤተሰብ ማእከልን መጎብኘት አለባቸው ወይም በቀን 24 ሰአት በሳምንት ለ 7 ቀናት በ (202) 399-7093 ላይ ይደውሉ።

## ከባድ የአየር ንብረት በሚሆንበት ጊዜ አንድ ሰው የሚቀዘቅዝበት ወይም ሙቀት የሚያገኝበት ስፍራ የት ሊያገኝ ይችላል?

- ከከባድ የአየር ንብረት መጠለያ የሚፈልጉ ግለሰቦች የዲሲ መጠለያ የስልክ መስመር 399-7093 ወይም 311 ላይ መደወል አለባቸው። የስልክ መስመሩ እንዴት ነጻ የማቀዝቀዣ ወይም የማሞቂያ ማእከል ጋር መገናኘት እንደሚቻል መረጃ አለው።
- ብዙ ጊዜ ማዕከላት በመዝናኛ ማእከሎች፣ ህዝባዊ ት/ቤቶች ወይም ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ይገኛሉ።

## በዚህ ውስጥ ያልተካተተ ጥያቄ አለኝ። ማንን ላነጋግር እችላለሁ?

የዲሲ መጠለያ የስልክ መስመርን በቀን 24 ሰአት በሳምንት ለ 7 ቀናት በ (202) 399-7093 ላይ ያግኙ።

*ይህ ገጽ የሸፈነው በእኛ— የዲሲ መንግስት— እና በእኛ ስራ ተቋራጮች በኩል የሚቀርቡ ሐብቶችን ብቻ ነው።*

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ፌብሩዋሪ 2021 ነው።*